# SMITTSKYDDSBLAD

## Patientinformation

Latent tuberkulos när behandling ges
Översatt till amarinja
Version 2022-04-11

## የሳንባ ነቀርሳ፥ ለበሽተኛ የሚሰጥ መረጃ

**የቅድሚያ መከላከል ህክምና የሚሰጥበት ግዜ። *የተላላፊ በሽታ ሓኪሞች መረጃ ልሳን።***

**የሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይተላለፋል?**
አንድ ሳምባ ነቀርሳ ያለበት ሰው፥ ቤት ውስጥ ሲስል በሽታውን ሌላ ሰው ላይ ሊተላለፍ ይችላል።  ሌላ የሰውነት አካል ውስጥ ያለ ሳንባ ነቀርሳ ኣና ያደባ ሳንባ ነቀርሳ አይተላለፉም። በልጅነት ዕድሜ ውስጥ ያሉ ልጆች በሽታውን ሲያስተላልፉ ማየት የተለመደ አይደለም። ሰዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ለምሳሌ በአንድ ቤት ውስጥ ለረጅም ግዜ አብረው የሚቆዩ ከሆነ፥ በሽታው ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው የመተላለፍ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

**ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?**
ነቀርሳው የተላለፈባቸው ሰዎች ሁሉ አይታመሙም። የብዙ ሰዎች ተፈጥሯዊ የበሽታ መከላከያ ኃይል ባክቴሪያው እንዳያድግና እንዳይሰራጭ ሊገታው ይችላል። በዚህ መልኩ ባክቲሬያው ሰውነት ውስጥ እያለ ኣድብቶ ይቀመጣል። በዚህ ሁኔታ የሚገኘው ነው **ያደባ ሳንባ ነቀርሳ** የሚባለው።

**ያደባ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ኣይደለም**
ከደም ምርመራ (IGRA-Test) ወይም ከቆዳ ምርመራ (Tuberkulintest) ካደረጉ በኋላ፥ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ኣለብዎት ከተባሉ **ሙሉ በሙሉ ጤነኛ** ነዎት ማለት ይቻላል። እናም በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ማጋባት ኣይችሉም።

ይሁን እንጂ በሕይወት እስካሉ ድረስ በሽታው አንድ ቀን ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት ይኖራል። ሆኖም ይህ የሚያጋጥምበት ዕድል በጣም የመነመነ ሰለሆነ ኣብዛኞዎቹ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች ህክምና ኣይደረግላቸውም።

**በአንዳንድ ሁኔታ የቅድመ መከላከል ህክምና ሊሰጥ ይችላል**
አንዳንድ ሰዎች ላይ በሽታው ኋላ ሊከሰትባችው ይችላል የሚል ስጋት በእጅጉ ካለ፥ የቅድመ መከላከል ህክምና እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ። ይህ ህክምና የሚደረገው በቅድሚያ ለህፃናትና ለታዳጊዎች ሲሆን ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያትም ይሰጣል። በተጨማሪም የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ኃይላቸው የተዳከመባቸው ለምሳሌ፥ የካንሰር ህክምና የሚያደርጉ፥ ኢንሱሊን የሚወስዱ የስኳር በሽተኞች፥ ከባድ የኩላሊት ችግር ያለባቸው ሰዎችም ይደረግላቸዋል።

አንዳንድ ጊዜ በቅርቡ የሳንባ ነቀርሳ ለያዛቸው ሰዎችም የቅድመ መካላከል ህክምና ይደረጋል።

**አስቀድሞ የመከላከል ህክምና እንዲያደርጉ ይመከራሉ**
ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ሲገኝብዎት በሽታው እንዳይከሰት በማሰብ ሃኪምዎ አስቀድሞ የመከላከያ ህክምና እንዲያደርጉ ሊመክርዎት ይችላል። የዚህ ምክረ ሃሳብ ዓላማ፣ ወደፊት በሳንባ ነቀርሳ በሽታ የመታመም ዕድልዎን ለመቀነስ ነው።

ምናልባት ወደፊት ረዘም ላለ ግዜ የሚቆይ (ሶስት ሳምንታት በላይ) የማሳል ሁኔታ፣ በሌሊት በላብ የመዘፈቅ ችግር፣ ትኩሳት ወይም ያልታለመደ የክብደት መቀነስ ከተከሰተ፥ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ እንዲደረግልዎት ሃኪምዎን መጠየቅ ይኖርብዎታል።

**የሚገኖኙት ሰው አድራሻና ተለፎን (Kontaktuppgifter)**

**የጤና ጣቢያው ሥም** *(Namn på mottagningen)*

………………………………………………………………………………

*ያገኙት ሰው ሥም (Du har träffat)*

ሃኪም *(Läkare)*………………………………………………..

ነርስ *(Sjuksköterska)*…………………………………………

የጤና ጣቢያው ቴሌፎን ቀጥር *(Telefonnummer/telefontid till mottagningen)*

…………………………………………………………………………..

SMITTSKYDD SKÅNE
040–33 71 80